**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**የሰ/መ/ቁ. 172365**

**ቀን ፡- ጥር 27 ቀን 2012 ዓ/ም**

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች** ፡- ደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ አክሲዮን ማህበር - ነ/ፈጅ አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- 1. አብርሃምና ደስታ ኮንስትራክሽን ሕብረት ሽርክና ማህበር
2. አቶ አብርሃም ሐዱሽ
2. አቶ ደስታ ገብረሕይወት
} በሌሉበት

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ያቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ ብድር ወስዶ ስላልከፈለ እና 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ማህበር አባል በመሆናቸው በውልና በንግድ ሕግ አንቀጽ 280 መሠረት የአንድነትና ነጣላ ኃላፊነት ስላለባቸው

ያልተከፈለ ዕዳ ብር 91,666.60 ከ15% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ዳኝነት የጠየቀበት ነው፡፡ ተጠሪዎች ክሱን መከላከል የሚያስችል ማስፈቀጃ ምክንያት እንዳላቸው ሲጠየቁ ክሱን አንከላከለውም ዕዳውን እናምንበታለን በማለት ለፍርድ ቤቱ ገልጸዋል፡፡

የመቐለ ከተማ ሠሜን ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከአመልካች ተበድረው ያልከፈሉትን ቀሪ ዕዳ ብር 91,666.60 ከተበደሩበት መጋቢት 15 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ በውሉ የተመለከተው ጊዜ እስከሚጠናቀቅበት መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ከ15% ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉና ከመጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ/ም ጀምሮ ውሉ ስለተቋረጠ በውሳኔው መሠረት እስኪፈጽሙ ድረስ ከ9% ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ አመልካች በወለድ አከፋፈሉ ላይ ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተጠሪዎች ጋር የገባነው ውል ወለዱ በ15% እንዲከፈል ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች ወለዱ በከፊል በ9% ሂሳብ እንዲከፈል መወሰናቸው ውሉን የማሻሻል ውጤት ያለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ወለዱ ግራቀኙ ከተስማማበት ውጭ በ9% እንዲታሰብ መወሰኑ ከፍ/ሕ/ቁ. 1731 አኳያ ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም በብድር ውሉ የተመለከተው ጊዜ መጠናቀቁ ስለወለድ አከፋፈሉ ያለው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ባቀረበው ክስ የጠየቀው ዳኝነት በውል መሠረት የብድር ገንዘብና ወለድ እንዲከፈለው ነው፡፡ ተጠሪዎች ክሱን መከላከል የሚያስችል ማስፈቀጃ ምክንያት እንዳላቸው ሲጠየቁ ክሱን አንከላከለውም ዕዳውን እናምንበታለን ያሉ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ሰፍሯል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 284 እና ተከታዮቹ መሠረት በአጭር ሥነ-ሥርዓት የሚቀርቡ ክሶች ብዙ ክርክር የማያስነሱና ተከሳሽ የሆነ ወገን ክሱን ለመከላከል ማስፈቀጃ ምክንያት ካላቀረበ ወይም ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ካልተቀበለው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 287 መሠረት ወዲያውኑ ለከሳሽ ፍርድ መሥጠት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ተጠሪዎች ክሱን ለመከላከል ማስፈቀጃ ምክንያት እንደሌላቸው እና ዕዳው ያለባቸው መሆኑን አምነው እያለ በክሱ መሠረት መወሰን ሲገባ የሥር ፍርድ ቤቶች የብድር ውሉ ጊዜ ካበቃ በኋላ ወለዱ መታሰብ ያለበት በሕጋዊ ወለድ በዓመት 9% ነው ማለታቸው የክርክር አመራር ግድፈት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል በግራቀኙ የተፈጸመው የብድር ውል በጊዜ የተከፋፈለ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በውሉ የተመለከተው ጊዜ ካለቀ በኂላ ውሉ እንደተቋረጠ ስለሚቆጠር በውሉ የተመለከተው የወለድ መጠን በዓመት 15% ሳይሆን ሕጋዊ ወለድ 9% ሊታሰብ ይገባል ብለዋል፡፡ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተመለከተው በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ የሚቆጠር እና ግራቀኙን የሚያስገድድ ነው፡፡ በብድር ውሉ የተመለከተው ጊዜ ተጠሪዎች ዕዳቸውን የሚመልሱበት ጊዜ ሲሆን ዕዳቸውን በውሉ በተመለከተው ጊዜ ካልከፈሉ አመልካች ክስ አቅርቦ ዕዳው እንዲከፈል ወይም ውሉ እንዲፈጸም የመጠየቅ መብት አለው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበውም በዚህ አግባብ ያልተከፈለ ዕዳ እንዲመለስለት ነው፡፡ የብድር መክፈያ ጊዜ ማለፉ ውሉ እንደተቋረጠ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ በአመልካች ሆነ በተጠሪዎች ውል እንዲቋረጥ የቀረበ ዳኝነት ሳይኖር ውሉ ተቋርጧል መባሉ የውል አተረጓጎም ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪዎች በውሉ በተመለከተው የመክፈያ ጊዜ ውስጥ ዕዳቸውን አለመክፈላቸው የወለድ መጠኑ እንዲቀነስላቸው የሚያደርግ ምክንያት አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ያለባቸውን ቀሪ እዳ ከፍለው እስኪያጠናቅቁ ድረስ በውሉ የተመለከተው የ15% ወለድ ሊታሰብ ይገባል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ብደሩን በከፊል በ9% ወለድ እንዲታሰብ መወሰኑ ሠዎች ያለባቸውን ግዴታ እንዳይወጡ የሚያበረታታና ውሉን የማሻሻል ውጤት ያለው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 106030 ሕዳር 05 ቀን 2011 ዓ/ም፣ የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 23805 የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ/ም እና የመቐለ ከተማ ሠሜን ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14758 ጥር 04 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪዎች ብር 91,666.60 ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ 15% ወለድ ጋር ለአመልካች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን እንዲችል ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የመቐለ ከተማ ሠሜን ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፋ/ዘ